# ዜና ስለ ራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት

ዜና ሰልፍ ሰፐላይ በየሁለት ወሩ አንዴ በ ሰልፍ ሰፐላይ ግብረ ሐይል በኢትዩጵያ አማካይነት የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም ግብረ ሐይል በመንግስት ተቋማትና ከልማት አጋሮች የተወጣጣ ሮረም ነው፡፡ የጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ዜና በማዘጋጀት ረገድ ቅድሚያውን ወስዷል፡፡

## ማውጫ

የመጀመሪያ ገፅ ቃለ ምልልስ

- ተቀራርበ መስራት ግዴታ ነው፡፡ከአቶ ሳሙኤል ታምሩ በደቡብ ክልል የውሃ መስኖ ልማት ቢሮ ሐላፊ

**በአቻ አጋሮች እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች**

- የማስተዋወቅ ገለፃ ለባለ 10000 የባለገመድ ፓምፕ /በጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት/
- የባለገመድ ፓምፕ ስፔስፋኬሽን /እና ስተዳዳረዳዜሽን/በጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት/
- ለአዲስ የፈጠራ በሰልፍ ሰፐላይ ዙሪያ የተዘጋጀ ቻሌንጅ ፈንድ /በሚሊንየም ዋተር አሊያንስ/
- በተለያዩ ሴክተር ቅንጅታዊ አሰራር ምን አልባትም በጋራ ሆኖ ለተመሳሳይ አላማ ለመስራት ዕድል ሊሆን ይችላል፡፡/በሚሊንየም ዋተር አሊያንስ/
- የባለ ገመድ ፓምፕ ተከላ ና ስልጠና አዲስ ለተመረጡ የአከባቢ ባለሙያዎች /ጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት/

## "ተቀራርበ መስራት ግዴታ ነው " ከአቶ ሳሙኤል ታምሩ በደቡብ ክልል የውሃ መስኖ ልማት ቢሮ ሐላፊ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ




አቶ ሳሙኤል ታምሩ በደቡብ ክልል ውሃ መስኖ ልማት ቢሮ ሐላፊ

ባለማቋረጥ ከሕብረተሰብ እየመጣ ያለውን ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ቁና የሆነ የባለድርሻ አካላት ድጋፍና የሴክተር መስሪያ ቤቶች አስተዋጾኦ ለራስ አገዝ ፕሮግራሞችን ለማቀጣጠል ወሳኝ ነው፡፡

ይላሉ አቶ ሳአሙኤል ታምሩ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ውሃና መስኖ ልማት ቢሮ ዋና ሐላፊ፡፡የራስ አገዝ ፕሮግራም በመጀመሪያ ደረጃ በሆኑ ቴክኖሎጂዎች ማገዝና መረዳት የኛም የመንግስት የልማት ዕቅድ አካል ነው፡፡

ይህንንም በተገቢው መንገድ ለመምራት የክልሉ ውሃና መስኖ ልማት ቢሮ ባሉት የዋሽ / WASH/ ሰንሰለቶች የማስተባበር ሚናዎ እየተዋጣ ይገኛል፡፡በሌላ መልኩ ደግሞ ያሉትን ሐብቶችንም ሆነ የተገኙ ልምዶችን በተገቢው መንገድ በአግባቡ መጠቀም የራስ አገዝ / Self Supply/ ፕሮግራሞች ዘላቂነት ባለው መንገድ ሽፋን ማግኘትና ማስተዋወቅ ይችላል፡፡

በትብብር መስራትን በተመለከት አቶ ሳአሙኤል ሲናገሩ በትብብር ከተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር መስራት ግዴታ ነው፡፡ሁላችንም እጅ ለ እጅ ተያይዘን ከተለያዩ መንግስት መስሪያ ቤቶች ማለትም ከውሃ ከጤና ከትምህርት ከግብርና ጋር በጋራ መስራት አለብን፡፡የራስ አገዝ ፕሮግራሞች ስኬት የሚለካውም ሆነ የሚሚረኮዘው በጋራ ግቦች ላይ ተግባብተን አልያም ተቀናጅተን ስንሰራ ነው፡፡ ጉዳዩ ከሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡እነዚህ የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ከአቅም ግንባታና ብቁ ባለሙያ በማፍራት ረገድ ዋነኛ ተቋሞቻችን ናቸው፡፡ ስለሆነም በቅንነት መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ በዛ ያሉ ችግሮችን እንደዚሁም ትምህርቶች አግኝተንባቸዋል፡ይላሉ አቶ ሳአሙኤል በክልሉ ስለተሰራጩት 10,000 የባለ ገመድ ፓምፖዎች ችግሮችና ተስፋዎች አስተያየታችውን ሲገልፁ እዚህም እዚያም ያሉ ችግሮች ማሰራጨቱንና የማስተካከሉን ሂደት ደካማ አድርጎብን ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን ስራዎችን ከጠንካራ መሰረት ለመጀመር ይህም በጎ ጎን አለው፡፡አንድ እንደ ትምህርት ያገኘነው በጎ ነገር ደረጃውን የጠበቀ ምርት አምርቶ ለመቀጠል ስራዎችን ማስተዋወቅ በሕብረተሰብ የሚፈጠሩትን የጥርጣሬና ያለመተማመን በሮችን ይዘጋል፡፡ (ቀጣዩ ገፅ ላይ ይቀጥላል)

በክልላችን ሁኔታ ግን ለስራው ተማኝ በሆኑ ሰራተኞች ድጋፍና ክትትል ስራዎች ወጥ በሆነ መንገድ እየተሰራ እና ዕድገት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ስለወደፊቱ ሲናገሩ አቶ ሳአሙኤል ይህን ብለውናል የራስ አገዝ ተቋማት ግንባታ በአንድ በተወሰነ ደረጃ ላይ መቆም የለበትም፡፡ቴክኖሎጂውና አቅም እስከፈቀደ ድረስ የተገኙትንም ግኝቶች ለሕብረተሰብ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡በመጨረሻም አቶ ሳአሙኤል በክልሉ ከሚገኝ የተለያዩ የልማት ተዋናዮች ጋር የተቀናጀ ተሳትፎ በማድረግ የክልሉን የውሃ ሽፋን በመጨመር የክላችን ሕብረተሰብ የኑሮ ደረጃ እናሻሽላለን በማለት መልዕክታቸውን በማስተላለፍ ቃለምልልሳቸውን አጠናቀዋል፡፡

## የ10000 ሺ የገመድ ፓምፕ ስርጭት በደቡብ

**WIDB/SNNPR, JICA WAS-RoPSS**

ከ18 ዞኖች 37 ወረዳዎች ከልዩ ወረዳዎች ከአስተዳደር ፣ ከግብርና ፣ ከጤና ፣ ከአሞ ማይክሮ ፋይናንስ የተወጣጡ ከ200 መቶ በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች በሀዋሳ በባለገመድ ፓምፕ ዙሪያ የማስተዋወቅና ስለአስተገባበሩ ውይይት አደረጉ፡፡

በተደረገው ውይይት ላይ የ10000 የባለ ገመድ ፓምፕ ስርጭትና ራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት በግልና የአካባቢ ንፅህና በባለገመድ ፓምፕ ከሚያመጣው ዘርፍ ቡዙ ጥቅሞች ዙሪያ ከልልሉ ውሃ ቢሮ እና ከዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት አባላት ማብራሪያና ገለፃ ተደርጓል፡፡ጎን ለጎንም የግል ኩባንያዎች ስለቤት ውስጥ የውሃ አጠባበቅና ህክምና ዙሪያ ምርቶቻቸውን ማስተዋወቅና ገለፃ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያየዘ ለተሳታፊዎች ስለአሞ ማይክሮ ፋይናንስ አሰራር ከዋስ ሮፕስ ጋር ያለውን ተሞክሮ ገለፃ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ተሳታፊዎቹ እርስ በእራሳቸው እንዴት ተቀናጅተው መስራት እንደልባቸው ውይይት አድርገዋል፡፡

# የባለገመድ ፓምፕ ደረጃ እና ዝርዝር ጉዳዮችን ማውጣት

**JICA WAS-RoPSS**



አቶ ቴዎድሮስ ታደለ የፕሮጀክቱ የሚያካሄዳቸው ስራዎች በመጎብኘት ላይ

እ.ኤ.አ ከታህሳስ 20 እስከ 22,2015 አቶ ቴዎድሮስ ታደለ በውሃ መስኖ ኤሌክትሪክ ሚኒስተር ኤሌክትሮ መካኒክ ሲሆኑ የገመድ ፓምፕ አሰራርን በአካል በመስክ ምልከታ ለመረዳት እና ዝርዝር ጉዳዮች ደረጃ ለማውጣት እንዲያመች በጌድዮ ዞን ይርጋጨፌ ወረዳ ተገኝተው የፓምፕን አሰራር ጎብኝቷል፡፡

በጉብኝታቸውም ከተጠቃሚዎች አከባቢ ባለሙያዎች አሰልጣኝ እና ሰልጣኝ ጋር ተወያይተዋል፡፡ በውይይታቸውም ስለዘላቂታማነቱ የህብረተሰብ አቀባበል በፓምፑ ደህንነት በፓምፑ ንፅህና ዙሪያ እና ጤና ውይይት አድርገዋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ የዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት ስራን ያደነቁ ሲሆን ለባለ ገመድ ፓምፕ ዝቅተኛ የሆነ የደረጃ ዝርዝር ወጥቶለት ቢፀድቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደረጃ ጠብቆ የባለ ገመድ ፓምፕ የተሻለ የጥራት ደረጃ ይዞ እንዲመረት አስተዋፆ ሊያበረክት እንደሚችል አስተያየታቸውን ሰጥቷል፡፡

ለባለ ገመድ ፓምፕ ዝቅተኛ ደረጃ ለማውጣት እንዲሁ ዝርዝሩን የያዘ የማመልከቻ ቅፅ በኢትዮጵያ ደረጃ ምዘናዎች ባለስልጣን ለተጨማሪ ቴክኒካዊ ፈተና እና ብሎም ዶክመንቱን ለማፅደቅ ቀጠሮ ተይዟል፡፡

## የፈጠራ ባለቤት ከሆኑ በራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት ዙሪያ የተዘጋጀ ቻሌንጅ ፈንድ ላይ ይሳተፉ

### Aqua For All

የግል ዘርፉን በራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት ላይ ለማጠናከር አላማ ያለው በአኳፎር ኦል/ Aqua for All/ የተዘጋጀ ፈንድ አቅርቧል፡፡ በዚህ ውድድር በግል ዘርፍ የሚሰሩና የራስ አገዝ ተያያዥነት ያላቸውን እንቅስቃሴዎችን የያዙ ሰዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡በሚሊኒየም ዋተር አሊያንስ የራስ አገዝ ቡድን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የግል ስራ ባለቤቶች በመጀመሪያ ኢላማ ተደርገዋል፡፡

## በአባወራ ደረጃ ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ለጋራ አላማ የተለያዩ ሴክተሮች በቅንጅት መስራት ጥሩ ዕድል ሊያመጣ ይችል ይሆን?

### Millennium Water Alliance

የተለያዩ የልማት ስራዎች በአባወራ ደረጃ ለሚካሆዱ ኢንቨስትመንቶች ሊያያዙ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በቤት ደረጃ የሚካሄዱ ኢንቨስትመንት የባለቤቱን ዕውቀትና ምንጮች ለራሳቸው የልማት ግንባታ ማበርከት ይገባቸዋል፡፡የማስተዋወቁና ድጋፍ የማድረግ ጉዳዮች ተመሳሳይ አቀራረብ እንዲኖራቸው ይገባል ምንም እንኳ የፋስሊቲ አይነቶች ቢኖሩትም፡፡

በአንድ ሴክተር የሚታዩ ችግሮችና መፍቴዎች ሌሎች በሴክተሩ ለሚገኙ ተዋንያኖች ልምድ ለመለዋወጥ ጠቃሚ ሲሆን በተጨማሪም ምን አልባትም በአንድ አባወራ ደረጃ ለሚደረጉ ስራዎች አብሮ መስራትንና ብሎም የሚገኙ ሀብቶችን በጋራ መጠቀም ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡

አንዳንድ በቤተሰብ ደረጃ የሚካሄዱ ኢንቬስትመንት ማለትም ለአባወራ ደረጃ የሚካሄዱ የመስኖ ስራዎች የባዮጋስ፣ የአከባቢ ንፅህና እና ራስ አገዝ የመጠጥ ውሀ ግንባታን ያጠቃልላል ፡፡

የተለያዩ ሴክተሮች የማስተዋወቅና ድጋፉ በማደርጉ እንቅስቃሴ ሀላፊነት አለባቸው ለምሳሌ በአባወራ ደረጃ የሚካሄዱ የመስኖ ስራ፣ በግብርና ሚኒስቴር የአካባቢ ንፅህና  በጤና ሚኒስቴር ፣ ባዮጋስ በኃይል እና ራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ግንባታ በውሃ ማዕድንና ኤሌክትሪክ ልማት ቢሮ በኩል የመተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡

ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ የሴክተሩ ተዋንያኖች በጋር የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ላይ ለመተግበር በሚያደርጉት ሂደት ውስጥ ለምሳሌ የአቅርቦት ሰንሰለት ፣ በአካባቢያቸው ሊገኝ የሚችል አገልግሎት ሰጪው ወዘተ ይመለከታል፡ለአብነት ያህል አፍሪካ ባዮጋዝ አጋርነት ፕሮግራም እየተደገፈ እና እየተሰራ ያለው የአባወራ የባዮ ጋዝ እንቅስቃሴ ዙሪያ እየተጠና ያለውን እንቅስቃሴ ስንመለከት ደካማ የሆነ የግል ሴክተሩ ተሳትፎ የብድር አገልግሎት አለመመቻቸት እና ደካማ የሆነ የባለድርሻ አካላት ለፕሮግራሙ ማሳያነት ሊነሱ የሚችሉ ችግሮች ናቸው፡፡

ውስን የሆነውን ሀብት በጋራ በአግባቡ በመጠቀም ተመሳሳይ የሆኑ ስራዎችን እንዳይሰሩ ከማገዙም በተጨማሪ በአባወራ ደረጃ የሚፈጠረውን ፍላጎትና አቅርቦት ለማጣጣም ከፍተኛ አስተዋጾኦ ያደርጋል፡፡በዚህም ዘርፍ በቅንጅት አሰራር መኖሩ ተነጣጥሎ የመተግበር ሩጫዎችን ይቀንሳል፡፡

ሀገር አቀፍ የራስ አገዝ ግብረ ሀይል እና ሳንቴሽን ማርኬትንግ መልቲ ስቴክ ሆልደር ፎረም እና መሰል  በአባወራ ደረጃ ለሚከናወኑ መስኖዎች እና የባዮጋዝ ልማት ስራዎችን በጋራ ወደ አንድ መድረክ ለማምጣት ጥሩ የሆነ አጋጣሚ እና ጥረቶችን ወደ አንድ ለማምጣት ያግዛል፡፡

# ለተመረጡ የአከባቢ ቴክኒሺያኖች የባለገመድ ፓምፕ ተከላ ስልጠና ተሰጠ

**JICA WAS-RoPSS**

ከይርጋጨፌ፣ዳሞትፑላሳናዳሌ ወረዳ አዲስ ለተመረጡ የአካባቢ ባለሙያዎች ለተከታታይ ስድስት ቀናት የገመድ ፓምፕ ተከላ ስልጠና በይርጋጨፌ ተሰጠ፤ሁለት የአከባቢ ቴክኒሻኖች በአንድ ቀበሌ በሚለው መረህ መሰረት ፕሮጀክቱ ተጨማሪ ጥቂት የአከባቢ ቴክኒሻኖችን ማሰልጠን ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡


የአቶ መልካሙ ታደለ የይርጋጨፌ ወረዳ ውሃ ቢሮ ሐላፊ በገመድ ፓምፕ ዙሪያ ገለፃ ሺሸጡ /ፎቶ በዋስ ሮፕስ/

እነዚህ የአከባቢ ቴክኒሻኖች ተጨማሪ እንደመሆናቸው ስልጠናው በአጭሩ ጊዜ ውስጥ የተካሄደ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ አዲስ ስልጣኞች ቀደም ብለው ከሰለጠኑ የአከባቢ ቴክኒሻኖች የበለጠ ልምዶችን እና ትምህርቶችን ይቀስማሉ ተባሎ ይጠበቃል፡፡

ይህ ስልጠና ስትራቴጂያዊ ለውጥ የተደረገበት ሲሆን ይህም ማለት ብዙ በመትከል ከሚገኝ ዕውቀት ይልቅ ጥቂት በመትከል የጠለቀ መረዳትን ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

በሁለት ባለገመድ ፓምፕ ዙሪያ የጠለቀ ዕውቀት ላላቸው አሰልጣኞች ማለትም አቶ አለነ ሀራዳ እና በአቶ ታረቀኝ ከወላይታሶዶ ቴክኒክ እና ሙያ በተሰጠው ስልጠና ፍፁም ቅንጅታዊ እና በተግባር ልምምድም የተሳካ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በዚህም ሰልጣኞች ፍፁም ደስተኛ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ለስልጠናው መሳካት የይርጋጨፌ ወረዳ ውሃ ቢሮ እና የወረዳው አሞ ማይክሮ ፋይናንስ ላሳዩት ቀና ትብብር ፕሮጀክቱ ምስገናውን እየገለፀ የእነዚህ ሁለት አካላት ቀና ትብብር ባይኖር ኖሮ ስልጠናውን በጊዜው መስጠት አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይታወቅ ነበር፡፡በዚህም ረገድ የይርጋጨፌ ወረዳ ውሃ ቢሮ ኃላፊ አቶ መልካሙ ታደለ የመስክ ምልከታ በማድረግ ተሳትፎአቸውን አሳይተዋል፡፡

በተያዘው የበጀት አመት ከማለፉ በፊት እነዚህ አዲስ የሰለጠኑ ሰልጣኞች ወደየመጡበት ሲመለሱ በፕሮጀክቱ ታርጌት ወረዳዎች ወደ ሥራ ይሰማራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ስልጠናው ከተጠናቀቀም በኃላ በየአከባቢያቸው የባለገመድ ፓምፖችን ዋጋ በመደራደር የመግጠም፣ የመጠገን እና መሰል ከባለገመድ ፓምፕ ጋር ተያያዥ ሥራ የመፍጠር እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡



የሬድዩሰር ብሎክ የተከላ ስልጠና በቴክኒክ እና ሙያ ተቋም መምህራን በአቶ ታረቀኝ (ፍትለፊት በስተቀኝ) (ፎቶ ከዋስ ሮፕስ)


የጥራት ቁጥጥር ከተከላ በኃላ በአቶ አለነ የጃይካ ዋስ ሮፕስ የቴክኒክ ረዳት

(ፎቶ በዋስ ሮፕስ)

# “በትብብር መንፈስ መስራት በጣም አስፈላጊ”

**JICA WAS-RoPSS**

የዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ከደቡብ ክልል ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ከደቡብ ክልል ውሃ መስኖ ልማት ቢሮ በመሆን ፕሮጀክቱ ከሚሰራቸው 4 ወረዳዎች ለተወጣጡ የባለ ድርሻ አካላት በእ.ኤ.አ ታህሳስ 4 እና 5 በሀዋሳ ሴንትራል ሆቴል የሁለት ቀን ስልጠና አዘጋጅቶ ነበር፡፡

የዋስ ሮፐስ ቡድንም ለክልሉ ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የገጠር ብድር ዋና ኦፊሰርና በመ/ቤቱ የፕሮጀክቱ ፎካል ስለ ስልጠናው ቃለ ምልልስ አድርገው ነበር፡፡



አቶ መኩሪያ መስቀሌ የገጠር ብድር ኦፍሰር (ፎቶ ዋስ ሮፐስ)

“ስልጠናው በቡዙ መልኩ ጠቃሚና አስፈላጊ ነበር”፡፡ይላሉ አቶ መኩሪያ ምንም እንኳ የስልጠናው ዋና ዓላማ ብድር አመላለስ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ቢሆንም የተፈጠረውን መድረክ ሌሎች የብድር አማራጮችን ለመንገር ተጠቅመንበታል ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተሰጠው ስልጠና ታች ላሉ ሰራተኞች በሚገባ ይረዳቸዋል ብለን እንምናለን፡፡

በተለይም በብድር አመላለስ ዙሪያ ያለው የተሳሳተ ግንዛቤ ያጠረዋል፡፡አሁን እንኳን ታች ካሉ ቢሮዎች እየመጡ ያሉ ግብረ መልሶች ስንመለከት በሁለቱ ቀን ስልጠናዎች ሰልጣኞች ትልቅ የሆነ ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ማየት ተችሏል፡፡

አቶ መኩሪያ ሲቀጥሉ “አሁን ካለፉት በተሻለ ከባለድረሻ አካላት ጋርመግባባት  እንደተፈጠረ እናምናለን እኛም እዚህ ከዋናው ቢሮ የተለያዩ ግምገማዎችን በየጊዜወ የምናደርግባቸው መንገዶች አሉን በዚህ በታችኛው መዋቀር ስለብድር አመላለስ እና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ እንወያያለን፡፡

አሁን የተሻለ እይታዎችንና ትኩረቶችን በባለገመድ ፓምፕ ዙሪያ ከክልል ው/መ/ል/ቢሮ በኩል የተገኘለት ሁኔታ አለ፡፡ እነዚህም ከጃይካ ልምዶችና ትምህርቶች ለመቀመር የተገኘ ነው፡፡አቶ መኩሪያ በክልሉ 10000 የባለ ገመድ ፓምፕ ስርጭት ያለውን ጠቀሜታ ሲናገሩ አሁን ዋናው ነገር አስፈላጊ የሆኑትን ልምዶች መውሰድና ተመሳሳይ የሆኑ ስህተቶች እንዳይፈጠሩ መድረግ ነው፡፡ አሁንም በብድር አመላለስ ዙሪያ ረዥም ርቀት መሄድ እንዳለብን እናውቃለን ፤ ከታችኛው መዋቅር እያገኘን ያለው ምላሽ አበረታች ቢሆንም ብዙ መስራት እንዳለብን ያሳያል፡፡

”በመጨረሻም አቶ መኩሪያ ቃለ ምልልሳቸውን ሲያጠቃልሉ “አንዳንዴ በስራዎች ዙሪያ የሚታዩ ቁርጠኝነት የማጣት ሁኔታ ይታያሉ፡፡ በተለይም የተለያዩ ሀላፊነቶችን በመከፋፈልና በመውጣት  ረገድ አንዱ አካል እንዲፈፅም የመጠበቅ ነገር ይታያል፡፡ይህ ደግሞ ስህተት ነው፡፡ሁላችንም የምንሰራቸውና የምንወጣቸው ኃላፊነቶች አሉን፡፡ያም ሆነ ይህ ሁላችንም ማወቅ ያለብን በትብብር መንፈስ የመስራት ጉዳይ ነው፡፡ይህም በጣም አስፈላጊያችን ነው፡፡



የመግቢያ ንግግር በዋስ ሮፐስ
(ፎቶ ዋስ ሮፐስ)



ጥልቅ የሆነ ውይይቶች በስልጠና ወቅት
(ፎቶ ዋስ ሮፐስ)



የቡድን ውይይት በስልጠና ወቅት
(ፎቶ በዋስ ሮፐስ)

## የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት ኤግዝብሽንና ሴሚናር 2016፡ እ.ኤ.አ ከመጋቢት 21-23

የራስ አገዝ ኤግዚብሽን ወይም ፎረም 2016 የአለም ውሃ ቀንን ምክንያት በማድረግ በሀገር አቀፍ የራስ አገዝ ግብር ሀይል ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ "የኔ ውሃ የኔ ስራ" በሚል መረህ የሚከበረው አለም አቀፍ የውሃ ቀን በሚገባ ከራስ አገዝ ፅንሰ ሐሳብ ጋር የሚሄድ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህ አመት የራስ አገዝ ግብረ ኃይል ብዙ አጋሮችን ማለትም በአባወራ ደረጃ እየተከናወኑ ባሉ ልማቶች ላይ ተሳታፊዎች ለምሳሌ በቤት መስኖ በቤት የሀይል አቅርቦት ላይ በሳንቴሽን ማርኬቲንግ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የእግዚብሽኑ እና ሴሚናሩ በራስ አገዝ ግንባታዎች ላይ ተሳታፊ ለሆኑ አካላት ሽልማት ተሰጥቷል፡፡ፕሮግራሙም እ.ኤ.አ. ከማርች 21 እስከ 23 2016 በውሃ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚኒስትር ቅጥር ጊቢ ውስጥ ይከናወናል፡፡የመጀመሪያው የራስ አገዝ ኤግዚብሽን እና ባዛር እ.ኤ.አ 2015 የአለም ውሃ ቀን ጋር ተያይዞ ከውሃ መስኖ እና ኤሌክትሪክ እንዲሁም ከራስ አገዝ የልማት አጋሮች ማለትም ሚሊንም ዋተር አሊያንስ፣ አኳ ፎር አል ፣ ከ ዋተር ዩት ኦርግ እና ጃይካ ዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት በትብብር አቅርበውታል፡፡ ለበለጠ መረጃ በየድርጅቶቹ ድህረ ገፅ ላይ መመልከት ይቻላል፡፡http://www.ircwash.org/news/my-water-my-business

### እ.ኤ.አ በታህሳስ 2016 እና በጥር 2016 የተከናወኑ ስራዎች

- ቻሌንጅ ፈንድ ዲዛይን ማድረግና ማስተዋወቅ ዘረፍ ፈጠራ አቅም ግንባታ ማድረግ
- የቤዝ ላይን ጥናት መጠናቀቅ በ
- የአማራ ብድን ቁጠባ ተቋም ከ ቪዥን ፈንድ ጋር ለአባወራዎች ብድር አሰጣጥ ዙሪያ የሚያደርጉት ውይይት / ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ/
- የገበያ ጥናት እና ምርት ማምረት በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም በአንዳንድ የራስ አገዝ አክሰሌሬሽን ፕሮጀክት በወራዳዎች /ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ/
- የባለ ገመድ ፓምፕ ኦረንቴሽን መስጠት የባለ ገመድ ፓምፕ የተከላ ስልጠና እና ድጋፍ ማድረግ
- የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ፕሮግረስ ስብሰባ
- የራስ አገዝ ገለፃ በ መልቲ ስቴክሆልደር ፎረም 7 በታህሳስ 2015 አዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል የአቶ ታመነ ሀይሉ ገለፃ በድርጅቱ ድህረ ገፅ ይገኛልhttp://www.ircwash.org/news/priority-one-wash-national-programme-%E2%80%93-focus-recent-multi-stakeholder-forum-ethiopia

### እ.ኤ.አ በየካቲት እና መጋቢት 2016 ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎች

- የራስ አገዝ ኤግዚብሽንና ባዛር ማስተናገድ (ከመጋቢት 21-23)
- ሚሊኒየም ዋትር አሊያንስ ፕሮጀክት የማነጅመንት ቡድን ስብሰባ የሰልፍ ሰፕላይ አክስለራሽን የትግበራ ዕቅድ ክለሳ
- በአባ ወራ ደረጃ ለሚሰራ የሰልፍ ሰፕላይ ፍላጎት መፍጠር ሚሊንየም ዋትር አሊያንስ በሚሰራቸው ወረዳዎች
- የባለ ገመድ ፓምፕን ማስተዋወቅና በአከባቢ ባለሙያዎች ተከላ ማድረግና እና ከማህበረሰብ ጋር ስብሰባዎችን ማከናወን፡፡/ዋስ-ሮፕስ/
- የ10000 የባለ ገመድ ፓምፕ በደቡብ ክልል ድጋፍ ማድረግና የተከላ ስልጠና መስጠት/ከዋስ ሮፕስ/
- የባለ ገመድ ፓምፕ የጥራት ቁጥጥር ለአምራቾች መስጠት /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/
- ለአከባቢ ባለሙያዎች የማነቃቂያ ስልጠና መሰጠት /ጃይካ ዋስ ሮፕስ/

If you have any comments, questions, suggestions, please contact us at;

JICA WAS-RoPSS Project
Room # 012, Ministry of Water, Irrigation and Energy
Tel: +251 - (0)11-651-1455
Mob: +251 - (0)935-353210/12/14
E-mail : jica.ropepump.ethiopia@gmail.com

Websites
JICA http://www.jica.go.jp/oda/project/1100485/index.html (Japanese)
http://www.jica.go.jp/project/english/ethiopia/004/index.html (English)
MoWIE http://www.mowr.gov.et/
IRC http://www.ircwash.org/
A4A http://www.aquaforall.org/
RWSN http://www.rural-water-supply.net/en/resources/details/662
IRC http://www.ircwash.org/